# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ <u>ከዚኽ ወዴት?</u>

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***<u>ክፍል አሥራ-ስድስት (ከክፍል አሥራ-አምስት የቀጠለ)፤-..</u>***

**ኢዴኃኅ....**

ሐ) ምሥረታ፤- የጉባዔው ተሣታፊዎች የአገሪቱን አጠቃላይ ሁኔታ እና ለለውጥ የቆሙ ሕዝባዊ (ዴሞክራት) ኃይሎች ቀደም-ሲል ትግላቸውን ለማስተባበር መሥርተዋቸው የነበሩ የጋራ መድረኮችን (ኅብረቶችን) ድክመቶች፣ ግድፈቶችና ጠንካራ ጎኖች በዝርዝር፣ በሰከነና በጥልቀት በመመርመር የጋራ ግንዛቤ ከጨበጡ በኋላ፤ አሁንም በተናጠል በሚያደርጉት ትግል ላይ መቀጠሉ ለአገራችንና ለሕዝቧ ሰቆቃ አለማክተም አስተዋፅዖ ከማድረግ ውጭ ስለማይሆን፣ ሁሉም አትራፊ የሚሆኑበትና አገርና ሕዝብን የሚጠቅም አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት አንድ ላይ መሠለፍ አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን በማጤንና በመቀበል፤ አልፎም ይኽንን አካል (ኢዴኃኅን) መሥርቶ ለመውጣት ሙሉ ስምምነት ላይ በመድረስ፣ ጉባዔው በመጨረሻ ሁለት ቀናት ስብሰባዎቹ የተወያየባቸው ነጥቦች የትግል ትልምንና ስልትን እንዲሁም የተደረሰባቸው ግንዛቤዎች ላይ የተመሠረተውን የጋራ ራዕይ በተግባር ለመተርጎም የሚያስችል መጣኝ አደረጃጀትን፣ አወቃቀርንና አስፈጻሚ አካላትን በዴሞክራሲያዊ ምርጫ መሰየምን በተመለከተ ነበር።

እንደሚታወቀው ቅድመ-ጉባዔም ሆነ በሂደቱም ጭምር አንዳንድ ወገኖች በጉባዔው ላይ የተሣተፉ ድርጅቶች ያሏቸውን ስብጥር (በአፈጣጠር፣ በታሪክ፣ በአቋም፣ በትግል ትልምና ስልት) ይዞታዎች ከላይ በማየት የጋራ የትግል ትልም ይዞና ሁሉም የሚስማሙበት የትግል ስልት ቀይሶ፣ ሁሉም ሊካተትበትና ሊገዛበት የሚችል አወቃቀርና መመሪያ አውጥቶ ተሣሥሮ በአንድ ላይ ለመታገል ስምምነት ላይ መድረስ አይቻልም የሚል ጠንከር ያለ ጥርጣሬ የነበራቸው መሆኑ አይካድም። ሆኖም ከልብ የታሰበበትና ሳይቻኮል ረዘም ያለ ጊዜ ተወስዶ የተደረገው ቅድመ-ዝግጅት ቢያንስ አብዛኛዎቹ ድርጅቶች በደንብ እንዲተዋወቁ፣ እንዲጠናኑና አመኔታን እንዲያሳድሩ ዕድል ስለ-ሰጠ፣ በኅብረተሰባችን ዘንድ “ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ” ከሚለው ግፊት ጀምሮ ተጨባጭ ውጤት የማየት የጋለ ፍላጎትና ጥባቆ ጋር ተደማምሮ ያሳደረው ጫና ድርጅቶች የነበራቸው ሥነ-ልቦናዊ ዝግጁነት እንዲጎለብትና ቁርጠኛ አቋም እንዲይዙ ተጨማሪ አስተዋፅዖ በማድረጉ የጉባዔው ተሣታፊዎች በወቅቱ አገርና ሕዝብን ያስቀደመ መርኅ-ተከል ስምምነት ላይ መድረስና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን መመሥረት ችለዋል።

ያም ሆኖ ኅብረቱን ለመመሥረት አስቸጋሪና ፈታኝ ችግሮች አልነበሩም ማለት አይደለም። ከተከሰቱት ዋነኛ እንቅፋቶች አንዱ የትግል ስልትን በተመለከተ ድርጅቶች የነበራቸው ልዩነት ነበር። የተወሰኑ ድርጅቶች በተለይም በአገር-ውስጥ “ሕጋዊ” ሆነው ከሚታገሉት መኻል “ሰላማዊ” ከሚባል ውጭ ምንም መስማት የማይፈልጉ ነበሩ። በሌላ በኩል በአገር-ውስጥ “ሕጋዊ” ሆነው በግልጥ የማይንቀሣቀሱና ይፋዊ እንቅስቃሴኣቸው በአብዛኛው በውጭ-አገሮች የሆነ በተለይም 'ትጥቅ ትግል እንካሂዳለን፣ መብታችንም ነው' የሚሉ ድርጅቶች በ“ሰላማዊ” ትግል ለውጥ ማምጣት ጨርሶ ስለማይቻል ቢያንስ “ሁለ-ገብ” ስልትን ከመከተል ሌላ አይሞከርም የሚል ጠንካራ አቋም የነበራቸው ነበሩ። በጉባዔ ደረጃ ብዙ ክርክር ከተደረገና ድርጅቶች በተናጠልና በቡድን በቡድን የጎንዮሽ አምኖ-የማሣመን ምክክሮችን በማድረግ እንዲሁም እያንዳንዱ የልዑክ ቡድን ጉዳዩን ከድርጅቱ ጋር እንዲመክር የተወሰነ ጊዜ ጭምር ተሰጥቶ ሁለቱን የተራራቁ አቋሞች ማቀራረብና አዲሱ የጋራ ድርጅት ኢዴኃኅ የሚያደርገው ትግል ሰላማዊ እንዲሆን መስማማት ተችሏል።

በጉባዔው የተሣተፉ ድርጅቶች ትግላቸው 'ሰላማዊ' እንዲሆን ሲወስኑ ከአንድ ዓመት ከአሥር ወራት በኋላ የሚደረገውን አገር-አቀፍ ምርጫ (ምርጫ-ዘጠና-ሰባትን) ዒላማ

ውስጥ አስገብተው መሆኑ ግልጥ ነበር። እዚኽ ላይ መታወቅ የሚኖርበትና ምናልባትም በቂ ግንዛቤ ያልተወሰደበት ሊሆን የሚችለው በሁሉም የኅብረቱ መሥራቾች ዘንድ በሰላማዊ ትግል ላይ እና ከሱም ጋር ተያይዞ ያለውን የምርጫ ፖለቲካን በተመለከተ የነበረው አመለካከት ከየድርጅቶች ታሪክና ጉዳዩን በንድፈ-አሣብ ደረጃ የመረዳት ሁኔታ ጥልቀት የጎደለው ወይም ሁሉም በአንድ የመግባቢያ ሞገድ ላይ አለመሆንና ሙሉ-በሙሉ መናበብ ያለመቻል ችግር ነበር ማለት እችላለሁ። ከኅብረቱ ምሥረታ በኋላ ብዙ ሣይርቅ በአባል ድርጅቶች መኻል ለከተከሰቱ ልዩነቶችም መንስዔ የሆነው ያ ግልጥ የግንዛቤ ጥራት ላይ ያለ ዝንፈትና ጉድለት ይመስለኛል።

መ) አደረጃጀት፤ ይኽ የጋራ ድርጅት ቀደም-ሲል ከተደረጉ የጋራ ጥረቶች ትምህርትን በመቅሰም አደረጃጀቱ መሠረተ-ሠፊና አግላይነት የሌለው መሆን እንደሚኖርበት በብዙዎች መኻል ቅድመ-ጉባዔ ስምምነትና ሙሉ እምነት ነበር። የጉባዔተኛው ስብጥር በራሱ ያን አቋም የበለጠ ያስረገጠና በጉባዔው ሂደት የተደረጉ ውይይቶችም በልዩነት አብሮ መሥራት እንደሚቻል አመኔታን ስላሳደረ፣ ኅብረቱ እንደታለመው ሁሉ ከኢሕአዴግ የተሻለ መሠረተ-ሠፊ አገር-አቀፍ ድርጅት የመሆኑ ጉዳይ ግልጥ ሊሆን ችሏል። ይኽ መሠረተ-ሠፊ ስብስብ ትኩረቱን በሚያለያዩ ነጥቦች ላይ ሣይሆን የትግሉ ዓይነታ ልዕለ-ግብ ወደ-ሆነው ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ግንባታ መንደርደሪያ በሚሆኑ ዋና ዋና የመግባቢያ ጉዳዮች ላይ ያደረገ፣ ሁሉም አባል ድርጅቶች 'እያንዳንዱ ለጋራው፣ የጋራው ለእያንዳንዱ' ጥቅም መቆም በሚችልበት ሁኔታ በሁሉም ደረጃ እኩል ተሣትፎ ማድረግ የሚችሉበት እንዲሆን የታመነበት፣ ጠንክሮ የተሠራበትና ትኩረት የተደረገበት ነበር። አደረጃጀቱ ወደ ዋናው ልዕለ-ግብ በሚደረገው ሂደት ድርጅቶች በመኻላቸው የተሻለ መግባባትና መተማመን እንዲዳብርና ቢያንስ አብዛኞዎቹ እስከ ውኅደት የሚያደርሣቸውን ሁኔታ የሚያመቻች እንዲሆንም በተገቢ ታስቦበታል። (ድርጅቶችን ወደ ውኅደት ለማምጣት ቀደም-ሲል ከተደረጉ የጎንዮሽና የቡድን ውይይቶችና ምክክሮች በመነሣት ወደ ጉባዔው አሥራ-አምስት ሆነን ስንገባ በጉባዔው መጨረሻ ላይ ቢያስ ወደ ሰባት እንጠቃለል ይሆናል፣ አልፎም በዓመትና ዓመት ተኩል ውስጥ ከሦስትና አራት ያልበለጠ ቁጥር እንዲኖረን ማድረግ ይቻላ የሚል እምነት የነበረን ሰዎች ነበርን)።

በኅብረቱ መሥራቾች ዘንድ ድርጅቶች ለሚገኙበት አደረጃጀት ዋና ምክንያት የሆነው በአገሪቱ ያለው አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ስለሆነ ማንም ድርጅት መታየትና ወደ-ኅብረቱ ለመግባት መመዘን  የሚኖርበት የግድ በተከተለው የአደረጃጀት ይዞታ ሣይሆን የጋራ ራዕዩን መቀበሉ፣ ችግሮችን በኢትዮጵያ ማእቀፍ ውስጥ ለመፍታት እንደሚቻል ማመኑና የጋራ አገራዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉም አትራፊ ለሚሆንበት አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት በጋራ ለመታገል ዝግጁነት ያለው መሆን እንደሚገባና ማንም እንዳይገለል ማድረጉ በመርኅ ደረጃ የተወሰደ አቋም ነበር። በዚያም ምክንያት ከአገር-ውስጥ/ከአገር-ውጭ፣ የብሔረሰብ/ኅብረ-ብሔረሰብ (ብሔራዊ)፣ የአካባቢ/አገር-አቀፍ፣ ወዘተ... ሣይባል በተቃዋሚው ጎራ የተሠለፈው ብቻ ሣይሆን በገዥው ክፍል ዙሪያ የተኮለኮሉም ሆኑ አዝማሚያው ያላቸው ሁሉ ሊሰባሰቡበት የሚችልና ሁሉም የሚካተቱበት  መሠረተ-ሠፊ አደረጃጀት እንዲኖረው ቁርጠኝነቱና ውሳኔው ነበር። በመሆኑም የኢዴኃኅ አደረጃጀት በአገሪቱ <u>ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ የሥርዓት ለውጥ</u> እንዲመጣ በሚደረገው ሕዝባዊ ትግል በአካሄዱም በመዳረሻውም (ግቡ) ሁሉም አባሎች በተስማሙበት የጋራ ራዕይ የሚመራ እንጂ እንደ ኢሕአዴግም ኅብረ-ብሔሰብና አገር-አቅፍ የሆኑ ድርጅቶችን በስሊት ያገለለና ለብሔረሰብ (ጎሣ) ድርጅቶች ብቻ የተከተረ፣ በኋላ እንደ-ተፈጠረው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (ቅንጅት) ደግሞ አቋም ወስዶ በአካባቢም ይሁን በብሔረሰብ (ጎሣ) ደረጃ የተመሠረቱትን ድርጅቶች ያገለለና አገር-አቀፍ ለሆኑ ብቻ የተወሰነ አልነበረም።

ሠ) አወቃቀር፤ ማንኛውም ድርጅታዊ አወቃቀር የድርጅቱን ራዕይ በተግባር ለመተርጎምና የታለመውን ግብ ለማስጨበጥ የሚያስችል መሣሪያ እንጂ መዋቅሩ በግልባጭ የድርጅቱን እምነት ገሪ ሊሆንም ይሁን የድርጅቱ ራዕይ ላይ ገዥነት ሊኖረው ጨርሶ አይገባም። ወይም

ወዋቅር ለግለ-ሰቦች እንዲመች ታስቦ የሚዘጋጁ መሆን አይኖርበትም። በመሆኑም የኢዴኃኅ አወቃቀር ሁሉን-አቀፍ መርኁንና የሚታገልለትን ራዕይ (አገራችን አንድነቷ የተከበረ፣ ዴሞክራሲያዊት፣ የበለፀገች፣ እኩልነት የሰፈነባት፣ የሕግ የበላይነት የተረጋገጠባት፣ መድብለ-ፓርቲ ሥርዓት እውን የሆነባት፣ ወዘተ.) የተከተለ መሆኑ የግድ ነበር። በዚኽ ጉዳይ ላይ ሠፊ ውይይት ተደርጓል። በአንድ ድርጅት (በኅብረሕዝብ-ኢትዮጵያ) ተነድፎ የቀረበው የድርጅቱ መዋቅር ከቀረቡት አማራጮች መኻል በድምፅ አልፎ ከአንዳንድ ማስተካከያዎች ጋር የኅብረቱ መዋቅር እንዲሆን ተደርጓል። ይኽ መዋቅር በአጭሩ ቀደም-ሲል የነበሩ የጋራ ጥረቶች የነበሯቸውን መዋቅራዊ ችግሮች ህሣቤ ውስጥ ያስገባ፣ የሕዝባችን ትግል መልክ ይዞ እንዲገፋ እና 'በአንድ-ሰው-አንድ-ድምፅ' መርኅ በአገራችን ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ ለማድረግ ሁኔታን በመፍጠር እውነተኛ መድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በእግሩ እንዲቆም ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚደረገው ሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል በውጭና በውስጥ ያሉ አባል ድርጅቶችን አስተሣስሮ መሠረተ-ሠፊነቱን እንደ-ጠበቀ የማስቀጠሉን አስፈላጊነት በደንብ ባጤነ መልኩ የተዘጋጀ ነበር።

የኅብረቱ መዋቅር ቀደም-ሲል ከነበሩት አወቃቀሮች ለየት የሚልባቸው ጎኖች እንዳሉት ግልጥ ነበር።

*አንደኛ* መዋቅሩ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች በአባልነት የሚታቀፉበትና ለጋራ ውሳኔ እንዲገዙ የሚያደርግ ብቻ ሣይሆን አባላት እንዲያከብሯቸው፣ ተግባራዊ እንዲያደርጓቸውና እንዲገዙባቸው የሚወጡ ውሳኔዎችን በሚያስተላልፉ አካላት ውስጥ በሁሉም ደረጃና እርከን የሚወከሉበት እንዲሆን የሚያስችል ነው። የድርጅቶች በኅብረቱ ውሳኔ-ሰጭ አካላት ውስጥ መወከላቸውም ሆነ በኅብረቱ ልዩ ልዩ ፈርጅ አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች የሚኖራቸው ተሣትፎ የሚወሰነው ለጊዜው በሚገኙበት ቦታ ብቻ መሆን ስለማይኖርበት ሕዝባዊ ትግሉ የጋራ እንደሆነ ሁሉ አወቃቀሩ ሁሉም አባል ድርጅቶች (በውጭ ይገኙ በውስጥ) እኩል ተሣትፎ፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርበታል። በመሆኑም የኅብረቱ መዋቅር ከእያንዳንዱ አባል ድርጅት ሁለት፣ ሁለት የአመራር አባላት የሚወከሉበት ብሔራዊ ሸንጎ፣ አንድ፣አንድ አባል የሚወከልበት የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ በየጽ/ቤቱ የሚቋቋሙ እያንዳንዳቸው ከአምስት ያላነሱ ቁጥር ያላቸው የብሔራዊ ሸንጎው ወይም የመሥራች ጉባዔ አባላት ወይም ለሚመደቡበት የተግባር ኮሚቴ እንደየ-ችሎታዎቻቸው አስተዋፅዖ ለማድረግ ብቃትና ችሎታ እንዳላቸው የታመነባቸው የአባል ድርጅቶች አባል የሆኑ ግለሰቦችን ያቀፉና እያንዳንዳቸው በአንድ (በአንዲት) የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም የብሔራዊ ሸንጎ አባል ኃላፊነት የሚመሩ ሰባት የተግባር ኮሚቴዎች (የውጭ ግንኙነት፣ የፋይናንስና ንብረት፣ የሕዝብ ግንኙነትና ማስታዎቂያ፣ የፖለቲካ ጉዳዮች፣ የድርጅቶች ጉዳይ፣ የልማትና የመልሶ ማቋቋም፣ እና የጥናትና ምርምር) እንዲኖሩት ተደርጎ ነው የተዋቀረው።

*ሁለተኛ* ኅብረቱ አንድ ሊቀ-መንበር፣ አንድ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ-መንበር ሦስት ምክትል ሊቀ-መንበሮች፣ አንድ ዋና-ፀሐፊ፣ ሁለት ምክትል ዋና-ፀሐፊዎች እና አንድ ረዳት ዋና-ፀሐፊ በድምሩ ፱ (ዘጠኝ) አባላትን ያቀፈ በብሔራዊ ሸንጎው የተሰየመ የሥራ-አመራር አካል አለው። ምንም እንኳን አባል ድርጅቶች ሁሉ በኅብረቱ እንቅስቃሴ እኩል ኃላፊነት፣ ተሣትፎና ተጠያቂነት ቢኖራቸውም በመዋቅሩ መሠረት ዋናው መሥሪያ-ቤት (ጽ/ቤት) እና አብዛኛው አመራር (ከዘጠኙ አምስቱ) አባላት (ሊቀ-መንበሩ፣ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ-መንበሩ፣ አንዱ ምክትል ሊቀ-መንበር፣ ዋና-ፀሐፊውና እረዳት ፀሐፊው) በአገር ውስጥ፣ በአንድ ምክትል ሊቀ-መንበርና በአንድ ምክትል-ዋና ፀሐፊ የሚመራ ጽ/ቤት በሰሜን አሜሪካ እና በተመሣሣይ ሁኔታ በአንድ ምክትል ሊቀ-መንበርና በአንድ ምክትል-ዋና ፀሐፊ የሚመራ ጽ/ቤት በአውሮጳ ይኖራል። (በዋና ጽ/ቤት ላይ ያልታሰበ እክል ቢገጥም የኅብረቱ የኃላፊነት እርከን በሰሜን-አሜሪካ የሚገኘው ጽ/ቤት፣ ከዚያም ቀጥሎ የአውሮጳው ይሆናል)። በዚኽ መሠረት ዋናው ጽ/ቤቱና አብዛኛው የበላይ አመራር በአገር-ውስጥ ሆኖ በአንድ በኩል ከአገር-ውጭ የሚገኙ ድርጅቶች በትግሉ የሚኖራቸው ተሣትፎ አንዳንዶች እንደ-ፈለጉት በተራ ስንቅ-አቀባይነት የተገደበ እንዳይሆንና በሙሉ አመኔታ እንዲንቀሣቀሱ፤ በውጭ አገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአንድ-መልክ ተደራጅተው ልዩ ልዩ አስተዋፅዖቻቸው አንድ-ወጥና ፍሬ የሚሰጡ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም በአገር-ውስጥ

ስለሚደረገው ትግል የውጭ መንግሥታትን ድጋፍ ለመሻት የሚደረገው ብዙ ዘርፍ ዘመቻ ተጠያቂነቱ፣ ኃላፊነቱና ቀጥተኛ ውክልናው ባላቸው ወገኖች አማካይነት ያለ-መዝረክረክ እንዲደረግ ለማስቻል፤ በሌላ በኩልም በውጭ የሚገኙ አባል ድርጅቶች በአገር-ውስጥ በመስክ ላይ ያሉ ድርጅቶች የኅብረቱን መተክሎችና ራዕዩን ተከትለው በራስ አነሣሽነት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ በውጭ የሚገኙት ያላስፈላጊ ጫና ሊያሳድሩ እንዳይችሉና ትግሉን እንዳይጎትቱ፣ በአጠቃላይ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ግን ሁሉም ተሣትፎ የሚያደርግበትን ሁኔታ ያመቻቸና ትሥሥሩ በብዙ ረድፎች ተቆላልፎ እንዲቀጥል የሚያደርግ ሆኖ ነው መዋቅሩ የተዘጋጀው፡፡

*ሦስተኛ* ቀደም-ሲል በነበሩ አወቃቀሮች የተሳተና ይኽ መዋቅር መልስ የሰጠበት ትግሉን መሠረተ-ሠፊ በማድረግ ረገድ የምሑራንን አስተዋፅዖና ተሣትፎ በተመለከተ ይሆናል፡፡ የኅብረቱ ትግል ዒላማ ተራ የመንግሥት ለውጥ ላይ ሣይሆን በአገራችን የሥርዓት ለውጥ እንዲመጣ ስለሆነ ማንም የመንግሥት ሥልጣን ይያዝ ማን ለአገራችን መሠረታዊ ችግሮች መፍትኄ ሊሰጡ የሚችሉ እርምጃዎች ሁሉ ሕዝብ የመከረባቸው፣ በደንብ የታሰበባቸውና በየዘርፉ ጥልቅ እውቀት ያላቸው ወገኖች በሚያደርጉት ሙያዊ ጥናት ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ስለሚያስፈልግ፤ ኢትዮጵያዊ አገር-ወዳድ ምሑራንን ማሣተፉ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል በምሑሩም ሆነ በፖለቲካ ድርጅቶች መኻል ያለው ግንኙነት አንድም በድርጅቶች በኩል በድርጅት አባልነት ከሚሣተፉት ውጭ ያሉትን ምሑራን የሚያገልል የሚያስመስልና ምሑሩ ክፍል ለሙያውና ለጥቅሙ ብቻ የቆመ አድርጎ የማየት፣ በምሑሩ በኩል ደግሞ በአገር ላይ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ትግል የ“ፖለቲከኞች” ብቻ አድርጎ የመውሰድና ሙያዊ አስተዋፅዖአቸውን ወደ-ኋላ ያዝ የማድረግና ደፈር-ብሎ ያለመሣተፍ አዝማመያዎች ስለነበሩ ግንኙነቱ እጅና-ጓንት የሚያሰኝ አለመሆኑ ይታወቃል፡፡ ይኽ 'ያልተፃፈ-ደንብ' መቆም እንዳለበትና ግንኙነቱ በአዲስ ምዕራፍ እንዲጀምር ማድረጉን መዋቅሩን ያዘጋጁት ያሰቡበት ይመስላል፡፡ ስለሆነም የኅብረቱ መዋቅር ምሑራን፣ በተለይም አገር-ወዳድና ዴሞክራት የሆኑ፣ ሠፊ አመለካከት ያላቸውና በሙያቸው አንቱ የተባሉ ምሑራን የግድ የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን ሣይጠበቅባቸው ሙያዊ የሆነ እውቀታቸውን ሊያካፍሉ የሚችሉበት ቀጥተኛ መዋቅራዊ መሥመር እንዲኖር በማለት ከሰባቱ የተግባር አካሎች (ኮሚቴዎች) ውስጥ አንዱ 'የጥናትና ምርምር' ክፍል ለዚሁ ጉዳይ የገባ የመዋቅሩ አካል ነው፡፡ ይኽ በአምስት፣ ማለት *የሕግና ሕገ-መንግሥት ጉዳይ፣ የኤኮኖሚ ጉዳይ፣ የሕዝብ ጤና ጉዳይ፣ የትምሕርት ጉዳይና የአገር መከላከያ ጉዳይ* ተብሎ የተመደበ ክፍል በታወቁ አገር ወዳድ ሊቃውንትና ባለሙያዎች የሚካሄዱና እያንዳንዳቸው ከአምስት ያላነሱ ቁጥር ያላቸው አባላትን ያቀፉ ናቸው፡፡ ይሁንናም በኅብረቱ ውስጥ በተከሰተው ልዩነት ሣቢያ የትኩረት አቅጣጫዎች በመዛባታቸው ከነዚኽ ውስጥ ከሁለቱ በስተቀር ከወረቀት ላይ ከመሥፈር በዘለለ ተግባራዊ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡

ሌላው በኅብረቱ መዋቅር ላይ እንዲጨመር የተደረገው አዲስ ክፍል *'አማካሪ ምክር ቤት'* በሚል የታወቀው አካል ነው፡፡ ይኽ ክፍል አባላት በኅብረቱ አባል ድርጅቶች ጠቋሚነት በብዙኀኑ አባል ድርጅቶች ተቀባይነት ያገኙ ከሰባት እስከ አስራ-አምስት ቁጥር ያላቸው የማንኛውም ድርጅት አባል ያልሆኑ በአመራርና በአስተዳደር ተመክሮ ያላቸው፣ ታዋቂ፣ የኅብረተሰቡን አክብሮት ያተረፉ፣ አገር-ወዳድ፣ አርቆ ተመልካች፣ አስተዋይና ሚዛናዊ አስተሳሰብ ያላቸው ግለሰብ ኢትዮጵያውያንን ያቀፈ የኅብረቱ አማካሪ አካል ነው፡፡ ይኽ ባሕላዊውን ከዘመናዊ አስተሣሰብ ያጣመረ አካል ታዛቢም፣ ሽምጋይም፣ አስታራቂም ገልጋይም በመሆን የኅብረቱን እንቅስቃሴ የሚታዘብና በየዓይነ-ቁራኛ የሚከታተል፣ በኅብረቱ አባል ድርጅቶች መኻል አለመጣጣሞችና አለመግባባቶች ወደ-ውጭ ወጥተው በአደባባይ መነታረኪያና መጨቃጨቂያ እንዳይሆኑ እንደ-አመጣጣቸው የሚያስተናግድ፣ ኅብረቱ አቅጣጫውን እንዳይስት የሚመክር፣ በኅብረቱና በአባል ድርጅቶች እንዲሁም በኅብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል አለመግባባት ሲከሰት ጉዳዩን በገለልተኝነት እያየ በሽምግልና የመፍትኄ አሳብ የሚሰጥ፣ ሲያስፈልግም ብያኔ የሚያሳልፍ አስታራቂ፣ አስማሚና ገላጋይ አካል ነው፡፡ ብይኑም የመጨረሻና በሁሉም ዘንድ ገዥነት አለው፡፡ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት .....***በክፍል አሥራ-ሰባት ይቀጥላል...***